# ዘመናዊ ትምህርትና ስልጣኔ - 2

## ምሁራን የዘመናዊ ትምህርት ሰለባ?

ከላይ እንደተጠቀሰው ዘመናዊ ትምህርት አሀዱ ብሎ አገር ውስጥ ሲገባ ባህልን መሰረት አድርጎ መጨመርን፣ መታከልን፣ ማዳበርን፣ የህዝብ ኑሮን መርዳትን ዓላማው አድርጎ ሳይሆን ማንነትን መለወጥን፣ ማሰልጠንን፣ መግራትን ከጭለማ "ነፃ" ማውጣትን አውሮፓዊ (Eurocentric view) መሰረት ላይ ተንተርሶ ስለሚገባ የእድገት መሰረቶችን ከማቅርቀዙ ጋር ከአፈሩና ከባህሉ ጋር መዋሃድ ተስኖት ችግር የማይፈታ ባዕድ ገላ ይሆናል;;

በሌላ አነጋገር የዘመናዊ ትምህርት መጀመሪያና መጨረሻ ኢትዮጵያን መሰረቱና ማዕከሉ ያደረገ ሳይሆን -የአውሮፓን የማህበራዊ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ህይወትና እድገት ሞዴሉ ያደረገ፣ ይህንንም እንዲያገለግል ሆኖ የተቀየሰ በመሆኑ ከኢትዮጵያ ራቁት ገላና ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ለማዋሃድ መሰረታዊና ቁልፍ አያያዥ ዘለበት ካልታከለበት ከጠቃሚነቱ ጋራ አፍራሽ ጎኑ እያየለ ይመጣል ;; ይህም የትምህርት ፖሊሲና ስርአትን የሚመለከት ይሆናል;;

ወደ ተማረው ክፍል ስንመለስ ምሁራኑ ወይም የልሂቃኑ በዘመናዊ ትምህርት ጋር አብሮ በሚገባው አመለካከት የተሰጣቸው ሚና ምእራባውያን ቅኝ ገዢዎች የለኮሱትን ችቦ ተቀብሎ መቀጠልና ጀምረው ያልጨረሱትን፣ ከግብ ያላደረሱትን የ"ማሰልጠን"ና የ"መግራት" "ነፃ" የማውጣት ተልዕኮ ተረክቦ መፈፀም ነው;; ይህን እንዲቀበሉ የሚያስገድዳቸው ማንም ሳይሆን ለምእራቡ ዓለም ያላቸው ከፍተኛ ፍቅር አምልኮትና ራሳቸውን ጨምሮ ለተቀረው በሙሉ ያላቸው ዝቅተኛ አመለካከት ነው;;

ለዚህም በቅድሚያ በትምህርት ሂደቱ ውስጥ ራሳቸውን ማሰልጠን መገራትና ነፃ ማውጣት ይጠበቅባቸዋል;; እነደ ነፃ አውጪው ፈረንጅ ማሰብ መመልከት እነደ ፈረንጅ እነደ ምእራቡ ሰው መሆን ይኖርባቸዋል;; የትምህርት ሂድቱም መነሻና መድረሻ መገልበጥ ኮፒ ማድረግ ይሆናል;; ከሳይንስ ትምህርቱ አንስቶ እስከ ጥቃቅኗ ተለምዶና ፋሽን ድረስ ያለው ሁሉ መገልበጥ አስፈላገ ይሆናል;; ቀለሙን መሽምደድ ባህሉን መገልበጥ የእለት ተለት ከዓመት እስከ ዓመት የተማሪዎች ቀለብና የዘመናዊ ትምህርት ተቋሞች መስፈርት ይሆናል;; ... መገልበጥ ራሱን የቻለ ዘመናዊ ትምህርት የቀመበት ባላና ምሶሶ ነው ;;

ከሰልጠናውም በሁዋላ ወደ ነባራዊው የስራው ዓለም ስምሪት ሲገባ ያ የተገለበጠ ኮፒ የታለመውን ሞዴል መሆን ያዳግተዋል;; በዚህ ላይ ነባራዊው ህይወት የሚያቀርባቸውን አዳዲስ ፈተናዎችና ችግሮች መፍትሄ ለመስጠትና ለመመከት የግልበጣ የአዕምሮ ዘይቤ (mind-set) ብቃቱ አጠራጣሪ ይሆናል;; በውጤቱም የአገር የፖሊቲካ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ህይወት ወዲያ ቅዝምዝም ወዲህ እየሆነ ችግሩ እየባሰ፣ ስልጣኔና እድገት እነደ ኮኮብ እየራቀ ያገር ሃብት ትርፍ የለሽ ኪሳራ ይሆናል;;

ከላይ በገለፅከት መጣጥፋ ዶ/ር መሳይ ከበደ እንዲህ ያብራራዋል;-

"...the grave consequence of the normativeness of the West, namely, the induction to copy Western ways. As imitators rather than creators, we become totally dependent, and hence lose our commitment and ability to think and act in a steadfast, creative, and consistent manner. Not only a copy never reaches the perfection of the model, but also the copyist has less passion and

commitment to execute the project. Since imitators already accept their inferiority and do not strive to deliver their own making, they fall short of being passionate and resolute about their undertaking. What they do is always very second-rate, if it is not deliberately messed up out of the naughtiness that is likely to come along when grownups and old cultures stoop to the status of children undergoing a process of domestication under Western tutorship. Modern schools are not learning places; they are where our intimate self assents to self-debasement and domestication"

ዘመናዊ ትምህርት አገራችን ስር ከሰደደ ግዜ ጀምሮ አብዛኛው የተማረው ክፍል ለአገራቸው ያላቸው ብርቱ ፍቅርና፣ የህዝባቸውን ህይወት ለመለወጥ ያላቸው የጋለ ስሜትና ፍላጎት ውስጣቸው እየጋመባቸው ጥርስ የሌለው አንበሳ ፍሬ የማይሰጥ አበባ ሆነው የቀሩትም በዚሁ እግር ተወርች ገንዞ በያዘ፣ ምሁሩ ላይ ከትውልድ ትውልድ ተሸጋግሮ በመጣ ደዌ - የአዕምሮ ቅኝ ተገዢነት ነው;; ይህ ያመረቀዘ በሽታም መድሃኒት እስከዛሬ ሳያገኝ አብዛኛውን የተማረ ክፍል ተስፋ አደብዝዞ የታዛቢነትና /passive/ የግብዝነት /cynical/ ባህል እንዲያዳብር አድርጓል;; ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ እንዲህ ሰል ይህን እውነታ ይታዘባል;-

"  3. ፍፁም ሰነፍና ጨለምተኛው ምሁራዊ ባህል ( Lazy and Cynical intellectual Culture)

- የደብተራ ባህል? እውቀት የሚሸመድድና ካለፈም ቴክኒካዊ እንጂ የተመራማሪውን ሂሳዊ አስተሳሰብ የሚያነፀባረቅበት አለመሆኑ

- እውቀት ከራስና ከማህበረሰቡ ህይወት ጋር ግንኙነት ያለው ባይሆንና ዝም ብሎ የኑሮ መደጎሚያ አድርጎ መውሰድ (የህግ ፣የፖለቲካ ሳይንስና፣ ወዘተ በምሳሌነት)

- ሥር የሰደደ የጨለምተኛነት (Cynical) አመለካከትና ይህንንም ጨለምተኛነት ለግለሰቡ ምሁራዊ ሰነፍና ( intellectual laziness ) መሸፈኛ አድርጎ መጠቀም

- የሙያተኝነት ሥሜት (Professionalism) መሞት መምህራን ስለ ትምህርት፣ ሀኪሞች ስለ ሕክምና፣ ጠበቆች ስለ ህግ … ወዘተ ያላቸው አመለካከትና በዚህ ሙያ ውስጥ ስለ እራሳቸው ያላቸው አመለካከት

- ይህ ሁሉ የፈጠረው የዝቅተኛነት ስሜት ምሁራን የማህበረሰቡን ችግሮች የሚያሳዩ፣ የወደፊት ኑሮው የተሻለ እንዲሆን የሚጠቁሙ ሀይሎች መሆናቸው ቀርቶ እንደማንኛውም ያልተማረ ዜጋ እርግ የተባሉትን የሚያደርጉ፣ ለራሳቸውና ለሙያቸው ብዙም ክብር የሌላቸው ደካማ ዜጎች መሆናቸውና በዚህም መላውን ሕብረተሰብ አብረው እነዳዳከሙት። " ይላል ከእስር ቤት በወጣ ማስታውሻው ላይ;;

እውቀት የመሸምደድ፣ የሙያተኝነት ስሜት መሞት፣ የጨለምተኛነት (Cynical) አመለካከት፣ የዝቅተኝነት ስሜት....ወዘተ የችግሩ ምንጭ ከላየ እነዳየነው ስር የሰደደ መሰረት አለው;;

በአገራችን አንድ በጥልቅ የሰፈነ አመለካከት የምሁራንን ላገራቸው እድገት ያለቸውን ሚናና አስተዋፅኦ ያመከነው የተፈጠሩት አምባገነናዊ መንግስታትና ስርአት ያደረሱት ጭቆና እነደሆነ ይነገራል;; ይህ የተወሰነ እውነታ ቢኖረውም መሰረታዊው ምክንያት ግን ሊሆን አይችልም;; በመጀመሪያ ከዘውዱ

አገዛዝ በስተቀር እነኚህ መንግስታትና ስርአቶች የፈጠራቸው ራሱ በዘመናዊው ትምህርት ስር ያለፈው የተማረው ክፍልና የርሱ የእጅ ስራ ውጤቶች ናቸው;; ለምን ሌላ የተለየ መንግስትና ስርአት ሊመጣ ወይም ለማምጣት አልቻለም? ለምነስ ተገቢውን ለውጥ ማምጣት አልተበቃም? የሚሉት መጠይቆች ጉዳዩን ወደራሱ ወደተማረው ክፍል ይመልሱታል;; ግን በርግጥ በዚህ አይነት የትምህርት ዓለም ታልፎ ሌላ የተሻለ ነገር ማመጣት ይቻል ነበርን? ... እነዳልተቻለና እነደማይቻል አሁንም ምክንያቱ ያው የቆየ በሽታ ያረጋግጣል;;

አምባገነናዊ አስተዳደር በኢትዮጵያም ሆነ በመሳሰሉት አገሮች የሚፈጥረው ጥንስሱና አሰኳሉ ያለው እዛው ዘመናዊ ት/ቤት ውስጥ ነው;; ለምእራቡ ያላቸው አምልኮና ነፃ ማውጣትን መግራትን ማሰለጠንን የሚለው የቅኝ ገዢዎች ርዕዮት አገር በቀል ቅኝ ገዢዎች እነዲሆኑ ከጧቱ ያዘጋጃቸዋል;; ከሳይንሱ ጋር የሚዋጠው መርዝ ቢረዱትም ባይረዱትም የምረቃው እለት ባጠለቁት ጥቁር ካባና ገዋን አምባገነንነትን ጠቅልለው ከት/ቤት ይዘው እነዲወጡ ያደርጋቸዋል;; እነሱ ሰልጥነው ተቀብተዋልና ለተቀረው ህብረተሰብ ያላቸው አመለካከት ምእራብ ቅኝ ገዢዎች ለተገዢ ህዝብ ያላቸውን አመለካከትና የአስተዳደር ስልት የተከተለ መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው;; እኛ እናውቅልሃለን፣ ከእኛ በላይ ላሳር - መርህ ይሆናሉ;;

ለቅርብ ምሳሌ ዛሬ በተቃዋሚው ጎራ የተሰለፉትን ድርጅቶች ውስጣዊ አሰራርና ገመና መቃኘቱ በቂ ይሆናል;; ዓላማ አድርገው ኢትዮጵያ ሊያመጡት የሚያወጁት ዲሞክራሲያዊ ስርአትና የድርጅታቸውን ህይወትና ያሰራር ባህርይ መመልከቱ ብዙ ብዙ ነገር ይነግረናል;; ብዙም ያሰተምራል;;

ይቀጥላል

ጃዊሳ